# አብይ የሰብአዊ ሥራዎች

## መለኪያ

# ጥራትንና ተጠያቂነትን የተመለከተ አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ

CAFOD Just one world
SCIAF Uniting to end poverty Caritas Scotland
Trōcaire Working for a just World.
CST Working Together

አሳታሚዎች: CHS Alliance፤ Group URD እና እስፌር ፕሮጀክት
የመጀመሪያ ዕትም: እ.አ.አ 2014
© ሁሉም መብቶች በህግ የተጠበቁ ናቸው። ለዚህ መመሪያ ይዘት የቅጂ ባለቤትነት መብት ያላቻው CHS አሊያንስ፤ Group URD እና እስፌር ፕሮጀክት ናቸው። መመሪያውን ለትምህርት አላማዎች ማለትም ለስልጠና፤ ለምርምርና ለፕሮግራም ሥራዎች ለማዋል ከተፈለገ እንደገና ተባዝቶ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፤ ይህም የሚቻለው ጥራትንና ተጠያቂነትን ለተመለከተ  አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ ዕውቅና ከተሰጠ ነው። ጥራትንና ተጠያቂነትን የተመለከተ አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያን በሙሉም ሆነ በከፊል ለመተርጎም ወይም ከነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ለመጠቀም በቅድሚያ የጽሁፍ ፈቃድ በኢሜይል አድራሻ info@corehumanitarianstandard.org. ጠይቆ ማግኘት የግድ ነው።

## NATIONAL PARTNERS IN ETHIOPIA:

የ CHS አማርኛ ትርጉም፣
CAFOD/SCIAF/Trocaire Working Together in Ethiopia, Action Aid, Christian Aid, Concern WW, Tearfund, እና Oxfam በጋራ በኢትዮጲያ በሚተገብሩት የ “Shifting the Power Through Building the Capacity of Local Organizations’ ፕሮጀክት ድጋፍ CHSን ለአገር በቀል ተቋማት እና ለማህበረሰቡ ቅርብ የሆኑ በሰብአዊ ድጋፍ ስራዎች ላይ ለተሰማሩ ባለድርሻ አካላት በሙሉ ተደራሽ ለማድረገ በሚል አላማ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሞዋል።
እ.አ.አ 2017

## መቅድም

ጥራትንና ተጠያቂነትን የተመለከተ አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ (CHS) የጆይንት እስታንዳርድ ኢኒሼቲቭ (JSI) ቀጥተኛ ውጤት ሲሆን ይኸውም ሂውማኒታሪያን አካውንተቢሊቲ ፓርትነርሺፕ (HAP) ኢንተርናሽናል፣ ፒፕል ኢን ኤይድ እና እስፌር ፕሮጀክት የአብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ ተጠቃሚዎች ዘንድ የበለጠ ወጥነት እንዲኖር አቅማቸውን በጋራ ያጣመሩበት ነው፡ ፡ JSI ከ2,000 በላይ በዋና ቢሮ፣ በክልሎችና ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ ሀገራት የሚገኙ የሰብአዊ እርዳታ ሰራተኞችን አማክሯል። የተገኘውም ግብረመልስ በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን ያማከለ እና ሰብአዊ መርሆችን መሰረት ያደረገ የእስታንዳርዶች ወጥነት አስፈላጊ መሆኑን አመላክቷል።

CHS ለ12 ወራት በሶስት ደረጃዎች የተካሄዱ ምክክሮች ውጤት ሲሆን የሰብአዊ እርዳታ ሰራተኞች፣ በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች፣ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ጥምረቶች፣ መንግስታት፣ የተባበሩት መንግስታትና ለጋሽ ተቋማት እንዲሁም ባለሙያዎች የCHS ይዘትን በጥልቀት የተነተኑ ሲሆን በዋና ቢሮና በመስክ ደረጃም ተፈትሿል።

ከእያንዳንዱ የምክክር መድረክ የተገኘው ግብረመልስ በሰብአዊ ተግባርና መለኪያ ዝግጅት መስክ የተለያየ የቴክኒክ እውቀት ያላቸውና ሰፊ አካላትን በሚወክሉ 65 አባላት ባሉት የቴክኒክ አማካሪ ቡድን ተገምግሞ ከለሳዎቹ ፀድቀዋል።

በሂውማኒታሪያን አካውንተቢሊቲ ፓርትነርሺፕ ኢንተርናሽናል፣ በፒፕል ኢን ኤይድ እና በእስፌር ፕሮጀክት ቦርዶች ይህ አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ እ.ኤ.አ በ2010 በ አካውንተቢሊቲ ፓርትነርሺፕ የተዘጋጀውን የተጠያቂነትና የጥራት አመራር መለኪያ፣ በፒፕል ኢን ኤይድ የተዘጋጀውን የአመራርና የእርዳታ ሰራተኞች ድጋፍ መልካም የአሰራር ህግ እና እስፌር ባዘጋጀው የመመሪያ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኘውን ስለአብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ የሚያትተውን ክፍል እንዲተካ የታሠበ ነው።

## ምስጋና

በ CHS ዝግጅት ሂደት የ CHS ረቂቆች ላይ ግብረመልስ በመስጠት፣ በድርጅታችሁ ውስጥ በተግባር በመፈተሽ ወይም የ CHS የምክክር ሂደቶችን በበላይነት በሚከታተሉ ቡድኖች ውስጥ በማገልገል የተሳተፉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ድርጅቶችን እና ግለሰቦችን እናመሰግናለን። በምክክርና በመፈተሽ ሂደት ወቅት በአደጋ የተጠቁ የተለያዩ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን ተሳትፎም በደስታ ተቀብለነዋል።

ሂውማኒታሪያን አካውንተቢሊቲ ፓርትነርሺፕ ኢንተርናሽናል፣ ፒፕል ኢን ኤይድ እና እስፌር ፕሮጀክት መለኪያዎችን ወጥ ለማድረግ ያደረጓቸውን ጥረቶች ግሩፕ ዩ.አር.ዲ. (Groupe URD) የተቀላቀለ ሲሆን እሱም የጥራት ኮምፓስ (Quality COMPAS) ማመሳከሪያ ማእቀፍ በ CHS ውስጥ እንዲካተት አድርጓል። የ CHS የቴክኒክ አማካሪ ቡድንና ንኡስ ቡድኑ የሆነው የቴክኒክ የበላይ ኮሚቴ የ CHS የምክክር ሂደቶችን በበላይነት የመምራትና በመጨረሻም በማፅደቅ ረገድ ሀላፊነቶችን ተወጥተዋል። የ CHS የፅሁፍ ቡድንም ከእያንዳንዱ የምክክር ምእራፍ የሚገኘውን ግብረመልስ በማካተት CHS ን የመከለስ ሀላፊነቱን ተወጥቷል።

የተደረሰባቸው ውጤቶች ሁሉን አካታች፣ ወካይና ሚዛናዊ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የ CHS የምክክር ሂደት በወልፍግሩፕ አማካሪዎች በነፃነት እንዲመቻች ተደርጓል። የቴክኒክ አማካሪ ቡድን፣ የቴክኒክ የበላይ ኮሚቴና የፅሁፍ ቡድን አባላት ሙሉ ዝርዝር www.corehumanitarianstandard.org ላይ ማግኘት ይቻላል። የእነሱ ያልተቆጠበ ድጋፍ ባይታከልበት ኖሮ የ CHS ምክክር ሥኬታማ አይሆንም ነበር።

የ CHS ሂደት በሚከተሉት ለጋሾች ከመደበኛ እና የፕሮጀክት ገንዘብ በለጋስነት ተደግፏል፡- የአውስትራሊያ መንግስት የውጭ ጉዳይና የንግድ ዲፓርትመንት፣ የካቶሊክ የውጭ ልማት ኤጀንሲ (CAFOD)፣ የዴንማርክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (Danida)፣ የጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ቢሮ፣ አይሪሽ ኤይድ (Irish Aid)፣ የስዊድን አለምአቀፍ የልማት ትብብር ኤጀንሲ፣የስዊዝ ልማት እና ትብብር ኤጀንሲ፣ የዩናይትድ ኪንግደም መንግስት ዩኬ ኤይድ እና የአሜሪካ መንግስት።

ሂውማኒታሪያን አካውንተቢሊቲ ፓርትነርሺፕ ኢንተርናሽናል፣ ፒፕል ኢን ኤይድ እና እስፌር ፕሮጀክት ለ CHS ዝግጅት ሂደት ላበረከቱት ገንዘብ አስተዋፅኦ ለሚከተሉት የቦርድ አባላት ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡- አክት አሊያንስ፣ አክሽን ኤይድ ኢንተርናሽናል፣ አክሽን ደችላንድ ህልፍት (Aktion Deutschland Hilft)፣ የብሪታኒያ ቀይ መስቀል፣ የካቶሊክ የውጭ ልማት ኤጀንሲ (CAFOD)፣ ኬር ኢንተርናሽናል፣ ክርስቲያን ኤይድ፣ ኮሙዩኒቲ ወርልድ ሰርቪስ ኢስያ፣ ዳንቸርችኤይድ፣ ሉተራን ወርልድ ፌዴሬሽን፣ ሴቭ ዘ ችልድረን ኢንተርናሽናል፣ ሴቭ ዘ ችልድረን ዩ.ኤስ እና ወርልድ ቪዥን ኢንተርናሽናል።

CHS ን በተግባር የፈተሹ ድርጅቶችን ሙሉ ዝርዝር www.corehumanitarianstandard.org ላይ ማግኘት ይቻላል።

## ግብረመልስ

CHS ን የተመለከቱ አስተያየቶችን በማንኛውም ጊዜ ለመቀበል ዝግጁ ነን። አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን ለ info@corehumanitarianstandard.org መላክ ይቻላል።

## ክለሳ

የተቀበልናቸውን አስተያየቶች በሙሉ እ.አ.አ ከታህሳስ 2019 በፊት በሚካሄደው የ CHS ክለሳ ወቅት ይስተናደጋሉ። CHS ን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ፣ ተያያዥ ምንጮችናን በዝግጅት ላይ የሚገኙ ሌሎች ሰነዶችን ለማግኘት እባክዎን www.corehumanitarianstandard.org ን ይጎብኙ።

## ትርጉሞችን የተመለከተ ማስታወሻ

CHS በአረብኛ፣ በፈረንሳይኛና በስፓኒሽ ቋንቋዎች የሚገኝ ሲሆን ወደ ተጨማሪ ቋንቋ መተርጎም የሚፈልጉ ከሆነ ትርጉምን የተመለከተ ማብራሪያ ከinfo@corehumanitarianstandard.org ያግኙ።

## ተያያዥ ሰነዶች

የ CHS አጠቃቀምን የሚያግዝ መመሪያና ስልቶችን ከwww.corehumanitarianstandard.org.በነፃ ማግኘት ይቻላል።

# ማውጫ


ሀ. መግቢያ 2 - 3

ለ. የጥራትንና ተጠያቂነትን የተመለከተ አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ (CHS) መዋቅር 5

ሐ. CHS ን መተግበር 6

መ. የይገባኛል ጥያቄዎች 6

ሠ. በመርህ ላይ የተመሰረተ ሰብአዊ ሥራዎች ትግበራ 7

ረ. ዘጠኝ ቃልኪዳኖችና የጥራት መስፈርቶች 8

ሰ. ቃልኪዳኖች፣ ተግባራትና ሀላፊነቶች 9-17

1. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ከፍላጎታቸው ጋር የተጣጣመና አግባብነት ያለው ድጋፍ ያገኛሉ 9
2. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የሚያስፈልጋቸውን ሰብአዊ ድጋፍ በትክክለኛው ጊዜ ያገኛሉ። 10
3. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች በተደረገላቸው ሰብአዊ ድጋፍ ምክንያት አሉታዊ ተፅዕኖ አይኖርባቸውም፤ ይበልጥ ዝግጁ፣ አይበገሬ እና የስጋት ተጋላጭነታቸው አነስተኛ ይሆናል። 11
4. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች መብቶቻቸውንና ድርሻዎቻቸውን ያውቃሉ፣ መረጃ ያገኛሉ እንዲሁም እነሱን በሚመለከቱ ውሳኔ አሰጣጦች ላይ ይሳተፋሉ። 12
5. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች አስተማማኝ፣ ምቹ ና ምላሽ ሰጪ የቅሬታ ማስተናገጃ ዘዴዎችን በቀላሉ ያገኛሉ። 13
6. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የተቀናጀና ተመጋጋቢ ድጋፍ ያገኛሉ። 14
7. ድርጅቶች ከልምዳቸውና ያለፈውን ከማስተዋል የሚማሩ እንደመሆናቸው በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የተሻለ የድጋፍ አቅርቦት ይደረግልናል ብለው ሊጠብቁ ይችላሉ። 15
8. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ብቁና ጥሩ አስተዳደር ካላቸው ሰራተኞችና በጎፈቃደኞች ድጋፍ ያገኛሉ። 16
9. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ድጋፍ የሚያደርጉላቸው ድርጅቶች ሀብቶችን በአግባቡ፣ ውጤታማነትና ስነምግባራዊነትን በተላበሰ መልኩ ይጠቀማሉ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። 17

ሸ. የቃላት መፍቻ 18

# ጥራትንና ተጠያቂነትን የተመለከተ አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ

## ሀ. መግቢያ

በየእለቱ በመላው አለም ከሁሉም የህይወት ዘርፍ የተውጣጡ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች አስፈላጊ የሆነ ሰብአዊ ምላሽ ለመስጠት ይንቀሳቀሳሉ፤ ይህም በየትኛውም ስፍራ የተከሰተን ሰብአዊ ስቃይ ለመከላከልና ለመቀነስ ካላቸው ፍላጎት የመነጨ ነው።

ጥራትንና ተጠያቂነትን የተመለከተው አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ (CHS) በሰብአዊ ምላሽ አሰጣጥ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚሰጡትን ድጋፍ ጥራትና ውጤታማነት ለማሻሻል ሊጠቀሟቸው የሚችሉ ዘጠኝ ቃልኪዳኖችን አስቀምጧል። ከዚህም በተጨማሪ በአደጋ ለተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የበለጠ ተጠያቂነትን አመቻችቶዋል፤ ይኸውም ሰብአዊ ድርጅቶቹ የገቧቸውን ቃልኪዳኖች መገንዘባቸው ድርጅቶቹን ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላቸዋል።

CHS በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን የሰብአዊ ሥራዎች ማእከል አድርጎ የሚወስድ ሲሆን መሰረታዊ ሰብአዊ መብቶቻቸው ይከበሩ ዘንድም ያበረታታል። ይኸውም አለምአቀፉን የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ  ጨምሮ በአለምአቀፍ ህግ የተደነገገውን በክብር በህይወት የመኖር መብትንና ከአደጋ የመጠበቅና በደህንነት የመኖር መብትን የሚያጠናክር ነው።

CHS እንደ አብይ መለኪያነቱ በመርህ ላይ የተመሰረተ፣ ተጠያቂነት ያለበትና ከፍተኛ ጥራት ያለው ሰብአዊ ተግባር ሊያሟላቸው የሚገቡ መሰረታዊ ይዘቶችን ያብራራል። ሰብአዊ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ከውስጣዊ አሰራሮቻቸው ጋር በማጣጣም በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ህግ አድርገው ሊጠቀሙት ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ ለአፈፃፀም ማረጋገጫነት መሰረት አድርገው ሊጠቀሙት የሚችሉ ሲሆን በተለያዩ ነባራዊ ሁኔታዎችና የድርጅት አይነቶች ጠቀሜታ ይኖረው ዘንድ ውስን ማእቀፍና ተያያዥ አመላካቾች ተዘጋጅተዋል።


CHS ሰብአዊ ተግባር በሚፈፅሙ ወይም አስተዋፅኦ በሚያበረክቱ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች፣ አስተባባሪ አካላት፣ ጥምረቶችና ሌሎች ቡድኖች ሊስፋፋ፣ ሊበረታታና ሊተገበር ይችላል። ምንም እንኳን CHS በቀዳሚነት ለሰብአዊ ሥራ ዘርፎች የታለመ ቢሆንም የትኛውም ድርጅት በአደጋ ከተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ጋር በተያያዘ የሚተገብራቸውን ስራዎች በሁሉም ገፅታዎች የተሻለ ጥራትና የበለጠ ተጠያቂነት ለማላበስ ሊገለገልበት ይችላል።

[2] አለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች መድበል አለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ፣ አለምአቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ቃልኪዳን እና አለምአቀፍ የሲቪልና የፖለቲካዊ መብቶች ቃልኪዳን እና በምርጫ የሚወሰዱ ፕሮቶኮሎችን ያካትታል።

CHS የአለም አቀፍ ምክክር ሂደት ውጤት ነው። የነባር ሰብአዊ ሥራዎች መለኪያዎችንና ቃልኪዳኖችን ቁልፍ ይዘቶች በአንድነት አሰባስቧል። ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ (በነዚህ ባይወሰንም) የሚከተሉት ናቸው፣-

- የአለምአቀፍ ቀይ መስቀል ማህበርና ቀይ ጨረቃ ንቅናቄ እንዲሁም ለአደጋ ደራሽ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የስነምግባር ደንብ
- እ.አ.አ በ2010 የተዘጋጀው ሂውማኒታሪያን አካውንተቢሊቲ ፓርትነርሺፕ (HAP) የተጠያቂነትና የጥራት አመራር መለኪያ
- የፒፕል ኢን ኤይድ የአመራርና የእርዳታ ሰራተኞች ድጋፍ መልካም የአሰራር ህግ
- የእስፌር አብይ መለኪያዎችና ሰብአዊ ቻርተር መመሪያ መፅሀፍ
- የጥራት ኮምፓስ (Quality COMPAS)
- የበይነ ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ በአደጋ የተጠቁ ህዝቦች የተጠያቂነት ቃልኪዳኖች (CAAPs)
- የኢኮኖሚያዊ ትብብርና ልማት ድርጅት (OECD) የልማት ድጋፍ ኮሚቴ (DAC) የልማትና ሰብአዊ ድጋፍ መመዘኛ መስፈርት

# ጥራትንና ተጠያቂነትን የተመለከተ አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ



# ለ. አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ መዋቅር

CHS በአደጋ ለተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የተገቡ ዘጠኝ ቃልኪዳኖች ስብስብ ሲሆን ሰብአዊ ድጋፍ ከሚያደርጉ ድርጅቶችና ግለሰቦች ምን መጠበቅ እንደሚችሉ ያትታል። እያንዳንዱ ቃልኪዳን በጥራት መስፈርት የተደገፈ ሲሆን ይህም በሰብአዊ ሥራዎች የተሠማሩ ድርጅቶችና ሠራተኞች ቃልኪዳኖቹን ለማሳካት እንዴት መስራት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው።

CHS የተዋቀረው ከዚህ በታች እንደተመለከተው ነው፥-

- ዘጠኝ ቃልኪዳኖች፣
- ደጋፊ የጥራት መስፈርቶች፣
- ቃልኪዳኖቹን ለማሳካት መተግበር ያለባቸው ቁልፍ ተግባራት፣ እና
- ቁልፍ ተግባራትን በመላው ድርጅት ውስጥ በወጥነትና በስርአት እንዲተገበሩ ለመደገፍ የሚያስችሉ ድርጅታዊ ሀላፊነቶች።

አብይ ተግባራትና ድርጅታዊ ሀላፊነቶች እንደየ ቅደም ተከተላቸው የሚከተሉትን ይገልፃሉ፥-

- በሰብአዊ ተግባር የተሰማሩ ሰራተኞች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ፕሮግራሞችን ለማሳካት ምን ተግባሮችን በወጥነት መፈፀም እንደሚገባቸውና ድጋፍ ለሚያደርጉላቸው አካላት እንዴት ተጠያቂ እንደሚሆኑ፤
- በሰብአዊ ተግባር የተሰማሩ ድርጅቶች ሰራተኞቻቸው ከፍተኛ ጥራት እና ተጠያቂነት ያለበት ሰብአዊ ድጋፍ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ በተጨባጭ ሊኖሯቸው የሚገቡ ፖሊሲዎች፣ ሂደቶችና ስርአቶች

በ CHS ውስጥ በጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት ውስን ፍቺ በዚህ ሰነድ ማብቂያ ላይ በቃላት መፍቻ መልክ ቀርቧል።

## ሐ. CHSን መተግበር

CHSን ለመጠቀም የወሰኑ ድርጅቶች ዘጠኙን ቃልኪዳኖች የማሳካት አላማ ይኖራቸዋል። እነሰ ከተባለም የሰብአዊ ምላሾቻቸውን ጥራትና ተጠያቂነት በቋሚነት ለማሻሻል የአሠራር ስርአቶቻቸውን፣ መዋቅሮቻቸውንና አሰራሮቻቸውን በወጥነት ለማሻሻል መስራት ይጠበቅባቸዋል። ነገር ግን በሰብአዊ ተግባር የተሰማሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች አይነታቸው ብዙ እንደ መሆኑ ወቅታዊ እርምጃ መውሰድ እና ከድርጅታቸው አቅምና ሀላፊነት እንዲሁም ከገጠማቸው የአደጋ ሁኔታና ደረጃ ጋር ተግባሮቻቸውን ማጣጣም አለባቸው።

ድርጅቶች ዘጠኙን ቃልኪዳኖች ለማሳካት ችግር በሚያጋጥማቸው ጊዜ እውነታውን መቀበልና እንቅፋት የሆነባቸውን ጉዳይ በምን መልኩ መፍታት እንሚኖርባቸው ማሰብ አለባቸው። ድርጅቶች ከእንደዚህ አይነት ሁኔታዎች መማርና የሚያጋጥሟቸውን ማነቆዎች የሚፈቱባቸውን ስልቶች ማዘጋጀት አለባቸው። CHSን በተግባር ለማዋል የሚካሄድ ማንኛውም ትንተና አብይ ተግባራትን በመከወን እና/ወይም ድርጅታዊ ሀላፊነቶችን በመወጣት ላይ ብቻ ሳይሆን የትኛውም ድርጅት ዘጠኙን ቃልኪዳኖች ለማሳካት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ስፋት ላይ መመስረት ይኖርበታል። ስለሆነም በ CHS የሚጠበቁ ቁልፍ ተግባራት ከነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በሚስማማ መልኩ መጣጣም ይኖርባቸዋል።

CHS ለሚከተሉት ድርጅቶችና ግለሰቦች ይሰራል፡-

- በአደጋ ለተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ቀጥተኛ ድጋፍ ለሚያቀርቡ፣
- በቀጥታ ድጋፍ በመስጠት ባይሳተፉም ለሌሎች ድርጅቶች ግን የገንዘብ፣ የቁሳቁስ ወይም የቴክኒክ ድጋፍ ለሚያደርጉ፣ ወይም
- ሁለቱንም አቀራረቦች አጣምረው ለሚሰሩ

CHS በሰብአዊ ሥራዎች የተሰማሩ አካላት በተለያዩ መልኮች እንዲጠቀሙበት ሆኖ የተቀረፀ ሲሆን፤ ከታች የተዘረዘሩትን ማሳካት እንዲያስችልም ጭምር ነው ፡-

- በአደጋ ለተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የበለጠ ተጠያቂነትን ለማመቻቸትና ለእነሱ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ጥራት ለማሻሻል፣
- ለ CHS የተሻለ ትግበራና ቀጣይነት ያለው መሻሻል የትግበራ እቅድ ማዘጋጀት፣
- ነባር ድርጅታዊና ቴክኒካል እስታንዳርዶችን ለመደገፍ CHSን  እንደማእቀፍ በመጠቀም ጥራትንና ተጠያቂነትን መከታተል፣
- ራስን መገምገምና የፕሮግራሞችን ጥራት ማሻሻል
- በተመሳሳይ አስተሳሰብ መመሪትን ለማረጋገጥ ወይም ለመመስከር እና ይህንን ለሌሎች በተግባር ለማሳየት
- እንደ አስፈላጊነቱ ውስጣዊ አሰራሮች እና ለሰራተኞች የሚደረጉ ድጋፎች በ CHS ውስጥ የተቀመጡ ተግባራትንና ድርጅታዊ ሀላፊነቶችን እንደሚያሟሉ ለመመዘን፣

CHSን ለመጠቀም የወሰኑ ድርጅቶች በድርጅታቸው ውስጥና በውጪ ለሚገኙ አካላት ማሳተዋወቅ ይጠበቅባቸዋል።
በአጋርነት የሚሰሩ ድርጅቶች ለ CHS ያላቸውን ቁርጠኝነት ማብራራት፣ አጋሮቻቸው  ለዘጠኙ ቃልኪዳኖች ያለቸውን አቀራረብ ለመረዳት መሞከርና የCHS ቃልኪዳኖችን በጋር ለመተግበር የሚችሉትን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

## መ. የይገባኛል ጥያቄዎች

በሰብአዊ ተግባር የተሰማራ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት CHSን  እንዲተገብርና አዛምዶ እንዲጠቀም የሚበረታታ ሲሆን "CHSን በተግባር ለማዋል እየሰራን እንገኛለን" ማለት ይችላል። ድርጅቶች CHSን እንከተላለን ለማለት ከመመዘኛው ጋር የተናበበ ሚዛናዊ ማረጋገጫ ማለፍ ይኖርባቸዋል።

[3] ፍቺውን ለማወቅ የቃላት መፍቻውን ይመከቱ

# ሠ. በመርህ ላይ የተመሰረተ የሰብአዊ ሥራዎች ትግበራ

ሰዎች የሰብአዊ ድጋፎች ዋነኛ ማጠንጠኛ ናቸው። ለአደጋ የሚሰጥ ማንኛውም ሰብአዊ ድጋፍ ቀዳሚ መነሻ ምክንያት ህይወት ማዳን፣ የሰዎችን ስቃይ መቀነስና በክብር የመኖር መብትን መደገፍ ነው።

ሰብአዊ ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶች ሰብአዊው አስገዳጅ ሁኔታ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ስለሚረዱ በየትኛውም ቦታ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሰብአዊ ድጋፍ መስጠት ይፈልጋሉ።

ሰብአዊ ተግባር በአራት ሰፊ ተቀባይነት ባላቸው መርሆች  ይመራል፡-

- ሰብአዊነት፡- በየትኛውም ስፍራ የሰው ልጅ ላይ የሚደርስ ስቃይ መፍትሄ ሊሰጠው ይገባል። የሰብአዊ ተግባር አላማ ህይወትንና ጤናን ለመከላከል እና የሰው ልጆችን ክብር ማረጋገጥ ነው።
- አለማዳላት፡- ሰብአዊ ተግባር ፍላጎትን ብቻ መሰረት አድርጎ መከናወን ይኖርበታል። ይህም ማለት በጣም አስቸኳይ ለሆኑ አስጨናቂ ክስተቶች ቅድሚያ መስጠትና በዜግነት፣ በዘር፣ በፆታ፣ በሀይማኖታዊ እምነት፣ ማህበራዊ መደብ ወይም ፖለቲካዊ አመለካከት ላይ የተመሰረተ አሉታዊ ልዩነት አለማድረግ ነው።
- ነፃነት፡- ሰብአዊ ተግባር ሰብአዊ ተግባሩ ከሚከናወንበት አካባቢ ጋር በተገናኘ ማንኛውም አካል ሊኖረው ከሚችል ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ ወይም ሌላ አይነት አላማ ነፃ መሆን አለበት።
- ገለልተኛነት፡- ሰብአዊ ተግባር የሚፈፅሙ አካላት በግጭቶች ውስጥ ወገን አለመለየትና በፖለቲካዊ፣ ዘር ነክ፣ ሀይማኖታዊ ወይም ርእዮተአለማዊ ይዘት ባላቸው ውዝግቦች ውስጥ መሳተፍ የለባቸውም።

ሰብአዊ መርሆች የሁሉም ሰብአዊ ስራ ማእከል ሆነው፤ሰብአዊ ተግባርን የሚመሩ ሲሆን አጠቃቀማቸውም ሰብአዊ ተግባርን ከሌላ አይነት ድርጊቶችና ተግባሮች ለመለየት ወሳኝ ነው። አራቱ መርሆች በ CHS ውስጥ በቃልኪዳኖች፣ በጥራት መስፈርቶች፣ በቁልፍ ተግባራትና በድርጅታዊ ሀላፊነቶች ውስጥ ተካትተዋል።


አለምአቀፍ የሰብአዊ ህግ፣ አለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ህግ እና አለምአቀፍ የስደተኛ ህግ ከግለሰቦችና ከቡድኖች ጥበቃ እና ሊደረግላቸው ከሚችለው ድጋፍ ጋር በተገናኘ መሰረታዊ የህግ እስታንዳርዶችን አስቀምጠዋል። የእስፌር ሰብአዊ ቻርተር በአደጋ ወይም በግጭት ከተጠቁ ወገኖች ደህንነት ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ያላቸውን ቁልፍ የህግ መርሆች በአጭሩ ጨምቆ አስቀምጧል። CHSን የሚተገብሩ አካላት በግዛታቸው ውስጥ በሚከሰቱ አደጋዎች ወይም በጦር መሳሪያ የታገዙ ግጭቶች ሰለባ ለሚሆኑ ሰዎች ጥበቃና ድጋፍ ማድረግ የመንግስታትና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለስልጣናት ቀዳሚ ሀላፊነት እንደሆነ ይገነዘባሉ። ሰብአዊ ተግባር እነዚህን ሀላፊነቶች መጋፋት የለበትም፤ ይልቁንም በሚቻልበት አጋጣሚ ሁሉ ማገዝ አለበት።

---

4 የሰብአዊነት፣ አለማዳላት፣ ነፃነትና ገለልተኛነት መርሆች የመነጩት ከሚከተሉት ነው፡- እ.አ.አ በ1965 በአለምአቀፍ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ 20ኛ አለምአቀፍ ኮንፈረንስ ላይ በቬየና የታወጀው የአለምአቀፍ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ንቅናቄ መሰረታዊ መርሆች፤ እ.አ.አ ታህሳስ 19/1991 የተደረገው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ 46/182፣ እና እ.አ.አ የካቲት 5/2004 የተደረገው የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ 58/114

5 አንዳንድ ድርጅቶች ከአድልዎ የፀዳ እርዳታ የመስጠትና በግጭቶች ውስጥ ወገን ያለመለመየት ቃልኪዳንን የሚያከብሩ ቢሆንም የገለልተኛነት መርህ ከተጠያቂነትና ከፍትህ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን በተመለከተ የማሳመን/አድቮኬሲመስራትን እንደሚከለክል አይገነዘቡም።

# ረ.  ዘጠኙ ቃልኪዳኖችና የጥራት መስፈርቶች



1.በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ከፍላጎታቸው ጋር የተጣጣመና አግባብነት ያለው ድጋፍ ያገኛሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ ከፍላጎት ጋር የተጣጣመና አግባብነት ያለው ነው።



2.በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የሚያስፈልጋቸውን ሰብአዊ ድጋፍ በትክክለኛው ጊዜ ያገኛሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ ውጤታማና ጊዜውን የጠበቀ ነው።



3. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች በተደረገላቸው ሰብአዊ ድጋፍ ምክንያት በአሉታዊ ተፅእና አሉታዊ ተፅዕኖ አይኖርባቸውም፤ ይበልጥ ዝግጁ፣ አይበገሬ እና የስጋት ተጋላጭነታቸው አነስተኛ ይሆናል፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ አካባቢያዊ አቅምን ያጠናከረና አሉታዊ ተፅእኖዎችን ያስወገደ ነው።



4. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች መብቶቻቸውንና ¾T>Ñv†"<" ድርሻዎቻቸውን ያውቃሉ፣ መረጃ ያገኛሉ እንዲሁም እነሱን በሚመለከቱ ውሳኔ አሰጣጦች ላይ ይሳተፋሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ በተግባቦት፣ ተሳትፎና ግብረመልስ ላይ የተመሰረተ ነው።



5. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች አስተማማኝ፣ ምቹ ና ምላሽ ሰጪ የቅሬታ ማስተናገጃ ዘዴዎችን በቀላሉ ያገኛሉ።

**የጥራት መስፈርት፡-** ቅሬታዎች ተቀባይነት ያገኛሉ፤ ተገቢ ምላሽም Ãc×†ªM። Ãc×†ªM።



6. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የተቀናጀና ተመጋጋቢ ድጋፍ  ያገኛሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ የተቀናጀና ተመጋጋቢ ነው።



7. ድርጅቶች ከልምዳቸውና ያለፈውን ከማስተዋል የሚማሩ እንደመሆናቸው በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የተሻለ የድጋፍ አቅርቦት ይደረግልናል ብለው ሊጠብቁ ይችላሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡-** የሰብአዊ ምላሽ ሰጪዎች በየጊዜው ከልምዳቸው ይማራሉ ፣ ይሻሻላሉ።



8.በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ብቁና በአግባቡ ከተደራጁ ሠራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች ድጋፍ ÁÑ—K<&

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰራተኞች ስራቸውን በውጤታማ መልኩ እንዲፈፅሙ ድጋፍ ማድረግና ፍትሀዊና ከአድሎ የፀዳ አያያዝ ይደረግላቸዋል



9. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ድጋፍ የሚያደርጉላቸው ድርጅቶች ሀብቶችን በአግባቡ፣ ውጤታማነትና ስነምግባራዊነትን በተላበሰ መልኩ ይጠቀማሉ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ።

**የጥራት መስፈርት፡-** ሀብቶችን በሃላፊነት በማስተዳደር እና በአግባቡ በመጠቀም ለታሰበላቸው አላማ ይውላሉ ።

# ሰ. ቃልኪዳኖች፣ ተግባራትና ሀላፊነቶች

## 1. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ከፍላጎታቸው ጋር የተጣጣመና አግባብነት ያለው ድጋፍ ያገኛሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ ከፍላጎት ጋር የተጣጣመና አግባብነት ያለው ነው።

አብይ ተግባራት

1.1 ነባራዊ ሁኔታውን እና ባለድርሻ አካላትን የተመለከቱ ትንተናዎችን ሥርአት ባለው፣ ሚዛናዊ በሆነ እና ቀጣይነት ባለው መለኩ ማካሄድ፣

1.2 የተለያዩ ቡድኖች[6] ፍላጎቶችን[7] እና ስጋቶችን ከአድልዎ በፀዳ ግምገማ ላይ ተመስርቶ እና ተጋላጭነቶቻቸውንና አቅሞቻቸውን በመረዳት ላይ የተመሰረቱ እና ተገቢ ፕሮግራሞችን መቅረፅና መተግበር፣

1.3 ፕሮግራሞችን ከተለዋዋጭ ፍላጎቶች፣ አቅሞችና ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ማስማማት።

ድርጅታዊ ሀላፊነቶች

1.4 በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን ፍላጎቶችና አቅሞች መሰረት ያደረገ ከአድልዎ የፀዳ ድጋፍ ለመስጠት ቁርጠኛ የሆኑ ፖሊሲዎች መኖር፤

1.5 ትኩረት የተነፈጉ ወይም የተገለሉ ሰዎችን ጨምሮ የማህበረሰቦችን ልዩነት ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡና የተሰባጠረ መረጃ መሰብሰብን የሚያስችሉ ፖሊሲዎች ላይ የተመሰረቱ ቃልኪዳኖች መኖር፤

1.6 ተገቢና ቀጣይነት ያለው የነባራዊ ሁኔታዎች ትንተና መካሄዱን የሚያረጋግጡ ሂደቶች መኖራቸው።

6 ይህ የሚከተሉትን ሊያመለክት ይችላል፤ ለምሳሌ ሴቶች፣ ወንዶች፣ ልጃገረዶች፣ ታዳጊ ወንዶች፣ ወጣቶችና አረጋውያን እንዲሁም አካልጉዳተኞችና አንዳንድ አናሳ ወይም የጎሳ ቡድኖች ላይ የተመሰረቱ ልዩነቶችን አለማድረግን

7 “ፍላጎቶች” እርዳታና ጥበቃን ያካትታል

## 2. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የሚያስፈልጋቸውን ሰብአዊ ድጋፍ በትክክለኛው ጊዜ ያገኛሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡- ሰብአዊ ምላሹ ውጤታማና ጊዜውን የጠበቀ መሆን፡፡**

**አብይ ተግባራት**

2.1 የታቀደው ተግባር ለማህበረሰቦቹ ተጨባጭ እና አስተማማኝ እንዲሆን ማነቆዎችን የሚፈቱ ፕሮግራሞችን መቅረፅ ፣[8]

2.2 በውሳኔ አሰጣጥና ትግበራ ላይ አላስፈላጊ መዘግየቶችን በማስወገድ ጊዜውን የጠበቀ ሰብአዊ ምላሽ መስጠት፣

2.3 ምላሽ ያላገኙ ማናቸውንም አይነት ፍላጎቶች አግባብነት ያለው የቴክኒክ አቅምና ሀላፊነት ወዳላቸው ድርጅቶች መምራት ወይም እነዚህ ፍላጎቶች ምላሽ እንዲያገኙ የማግባባት/የአድቮከሲ ስራ መስራት፣

2.4 ፕሮግራሞችን ለመቅረፅ እና ለመገምገም በሰብአዊ ሥራዎች ዘርፍ ውስጥ አግባብነት ያላቸው የቴክኒክ እስታንዳርዶችንና መልካም አሰራሮችን መጠቀም፣

2.5 ፕሮግራሞችን ለማስማማትና ዝቅተኛ አፈፃፀምን ለመቅረፍ የሰብአዊ ምላሽ ስራዎችን፣ ሂደቶችንና ውጤቶችን መከታተል

**ድርጅታዊ ሀላፊነቶች**

2.6 የፕሮግራም ቃልኪዳኖች ከድርጅታዊ አቅሞች ጋር መጣጣም

2.7 የፖሊሲ ቃልኪዳኖች የሚከተሉትን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል፡-

ሀ. በስራዎችና በአመጡት ውጤት ላይ የሚካሄድ ሥርአታዊ፣ ሚዛናዊና ቀጣይነት ያለው ክትትልና ግምገማ

ለ. ከክትትልና ግምገማ የሚገኝ ተጨባጭ መረጃ ፕሮግራሞችን ለማስማማትና ለማሻሻል ማዋል

ሐ. አስፈላጊውን ግብአት አብሮ በመመደብ ውሳኔዎችን በወቅቱ መስጠት

8 ለምሳሌ ሰብአዊ ተደራሽነት፣ ደህንነት፣ ሎጂስቲክስና ፈንድ

## 3. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች በተደረገላቸው ሰብአዊ ድጋፍ ምክንያት አሉታዊ ተፅዕኖ አይኖርባቸውም፤ ይበልጥ ዝግጁ፣ አይበገሬ እና የስጋት ተጋላጭነታቸው አነስተኛ ይሆናል፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ አካባቢያዊ አቅምን ያጠናከረና አሉታዊ ተፅእኖዎችን ያስወገደ ነው።

አብይ ተግባራት

3.1 ፕሮግራሞች በአካባቢያዊ አቅሞች ላይ መመስረታቸውን ማረጋገጥና በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን አይበገሬነት(resiliance) በማሻሻል ላይ አተኩሮ መስራት

3.2 ማንኛውም አይነት ነባር የማህበረሰብ አደጋና ስጋት ግምገማ ውጤቶች እና የዝግጁነት እቅዶችን ስራዎችን ለመምራት መጠቀም፣

3.3 ለወደፊት አደጋዎች በሚከሰቱበት ወቅት ቀዳሚ ምላሽ ሰጪ ሆነው እንዲገኙ ለማብቃት የአካባቢውን አመራርና ድርጅቶች አቅም ማሳደግ፤ ትኩረት ያላገኙና የተገለሉ ቡድኖች በአግባቡ መወከላቸውን ለማረጋገጥ እርምጃዎችን በመውሰድ፣

3.4 የረጅም ጊዜ አዎንታዊ ተፅእኖን ከወዲሁ ለማረጋገጥና የጥገኝነት ስጋትን ለመቀነስ በሰብአዊ ፕሮግራሙ ጅማሬ ላይ የሽግግር ወይም አጠናቅቆ የመውጫ ስልቶችን ማቀድ፣

3.5 በቶሎ ከአደጋ ለማገገም የሚያስችሉና የአካባቢውን ኢኮኖሚ የሚጠቅሙ ፕሮግራሞችን መቅረፅና መተግበር፣

3.6 ሊከሰቱ የሚችሉ ወይም የተከሰቱ ያልታሰቡ አሉታዊ ውጤቶችን በወቅቱና ስልታዊ በሆነ መልኩ መለየትና እርምጃ መውሰድ፤ የሚከተሉትን ጨምሮ፡-

ሀ. የሰዎች ደህንነት፣ ክብርና መብቶች
ለ. በሰራተኞች የሚፈፀም የወሲብ ብዝበዛና ጥቃት
ሐ. ባህል፣ ፆታ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነቶች
መ. የኑሮ መተዳደሪያ
ሠ. የአካባቢው ኢኮኖሚ እና
ረ. አካባቢ

ድርጅታዊ ሀላፊነቶች

3.7 ፖሊሲዎች፣ እስትራቴጂዎችና መመሪያዎች የሚከተሉትን ለማስፈፀም ይቀረፃሉ፡-
ሀ. ማንኛውም አይነት አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትሉ ፕሮግራሞችን መከላከል፤ ለምሳሌ በሰራተኞች አማካኝነት በአደጋ በተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ላይ የሚፈፀም ብዝበዛ፣ ጥቃት ወይም አድልዎ
ለ. አካባቢያዊ አቅሞችን ማጠናከር

3.8 በአደጋ ከተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የሚሰበሰብና እነሱን ለአደጋ ሊያጋልጥ የሚችል ማንኛውም አይነት ግለሰባዊ መረጃን መጠበቅ የሚያስችሉ ስርአቶችን አዘጋጅቶ ማስቀመጥ

## 4. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች መብቶቻቸውንና ¾T>Ñv†¨<” ድርሻዎች ያውቃሉ፣ መረጃ ያገኛሉ እንዲሁም እነሱን በሚመለከቱ ውሳኔ አሰጣጦች ላይ ይሳተፋሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ በተግባቦት፣ ተሳትፎና ግብረመልስ ላይ የተመሰረተ መሆን፡፡

አብይ ተግባራት

4.1 ስለድርጅቱ፣ ስለሚመራባቸው መርሆች፣ ከሰራተኞቹ ስለሚጠብቃቸው ባህሪያት፣ ስለሚተገብራቸው ፕሮግራሞች እና ምን አስተውዖ ለማበርከት እንደሚፈልጉ በአደጋ ለተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች መረጃ መስጠት፣

4.2 የተለያዩ የማህበረሰብ አባላት በተለይም ተጋላጭና የተገለሉ ቡድኖች በቀላሉ መረዳት በሚችሏቸው፣ አክብሮታዊ በሆኑና ባህሉን በጠበቁ ቋንቋዎች፣ ስልቶችና ሚዲያ መልዕክቶችን ማስተላለፍ፣

4.3 በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን ተሳትፎና መስተጋብር በሁሉም የስራ ምእራፎች በማካተት የውክልናውን አካታችነት ማረጋገጥ፡፡

4.4 ለፆታ፣ ለእድሜና ለግብረ መልስ ሰጪዎች ስብጥር ልዩ ትኩረት በመስጠት በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች በተደረገላቸው እርዳታ ጥራትና ውጤታማነት ላይ የተሰማቸውን የእርካታ ደረጃ በተመለከተ ግብረመልስ እንዲሰጡ ማበረታትና ማመቻቸት፣

ድርጅታዊ ሀላፊነቶች

4.5 መረጃ ማጋራትን የተመለከቱ ፖሊሲዎች መኖር እና ግልፅ የሆኑ የግንኙነት ባህሎችን ማዳበር፣

4.6 በሁሉም የስራ ምእራፎች ውስጥ የለዩዋቸውን ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችና ስጋቶች በሚያንፀባርቅ መልኩ በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን የሚያሳትፉ ፖሊሲዎች ተዘጋጅተው መቅረብ፣

4.7በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን አክብሮት የሚገባቸው የሰው ልጆች አድርጎ በሚያቀርብ መልኩ ውጫዊ ግንኙነቶችን ገንዘብ ለማሰባሰብ የዋሉትን ጨምሮ ትክክለኛ፣ ስነምግባራዊና አክብሮታዊ መሆን አለባቸው፤

## 5. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች አስተማማኝ፣ ምቹ ና ምላሽ ሰጪ የቅሬታ ማስተናገጃ ዘዴዎችን በቀላሉ ያገኛሉ፤

**የጥራት መስፈርት፡-** ቅሬታዎች ተቀባይነት ያገኛሉ፤ ተገቢ ምላሽም ይሰጣቸዋል

አብይ ተግባራት

5.1 በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦች ቅሬታ የሚስተናገድበት ሂደትን በተመለከተ በቀረፃ፣ ትግበራና ክትትል ሂደቶች ላይ ማማከር፣

5.2 ቅሬታዎችን ተቀብሎ ማስተናገድ፤ እና አሰራሩን እንዴት መጠቀም እንደሚቻልና የሚስተናገዱ ጉዳዮችን ገደብ ማስረዳት፣

5.3 ለቅሬታ አቅራቢዎችና በሁሉም ምእራፎች ተጠቂ ለሆኑ አካላት ደህንነት ቅድሚያ በሚሰጥ መልኩ ቅሬታዎችን በወቅቱ፣ በፍትሀዊነት እና አግባብነት ባለው መንገድ ማስተናገድ፣

ድርጅታዊ ሀላፊነቶች

5.4 በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችንና ህዝቦችን ቅሬታዎች ማስተናገጃ አሰራርን በአግባቡ ማደራጀት እና ማስቀመጥ። የቅሬታዎች ማስተናገጃ አሰራሩ ፕሮግራምን፣ ወሲባዊ ብዝበዛን፣ ጥቃትንና ስልጣንን ያለአግባብ መጠቀምን ማካተት አለበት፣

5.5 ለቅሬታዎች ተገቢውን ትኩረት መስጠት እና በተቀመጡ ፖሊሲዎችና አሰራሮች መሰረት እርምጃ የሚወስድ ድርጅታዊ ባህል መገንባት፣

5.6 ወሲባዊ ብዝበዛንና ጥቃትን መከላከል በተመለከተ ድርጅቱ የገባቸውን ቃልኪዳኖች ጨምሮ ከሰብአዊ ሰራተኞች ስለሚጠበቁ ባህሪያት በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ሙሉ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

5.7ከድርጅቱ የሀላፊነት ገደብ ውጪ የሆኑ ቅሬታዎችን መልካም አሰራርን በጠበቀ መልኩ ወደሚመለከተው አካል መምራት።

## 6. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የተቀናጀና ተመጋጋቢ ድጋፍ ያገኛሉ።

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰብአዊ ምላሹ የተቀናጀና ተመጋጋቢ ነው።

አብይ ተግባራት

6.1 የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ሚናዎች፣ ሀላፊነቶች፣ አቅሞችና ፍላጎቶች መለየት [9]፣

6.2 የሰብአዊ ድጋፍ ምላሹ ከብሄራዊና አካባቢያዊ ባለስልጣኖች[10] እና ከሌሎች ሰብአዊ ድርጅቶች ጋር መደጋገፉን ማረጋገጥ፣

6.3 አስፈላጊ በሆኑ የማስተባበሪያ መድረኮች ውስጥ መሳተፍና ከሌሎች ጋር መተባበር የሰፊውን ሰብአዊ ድጋፍ ጥረት ሽፋንና አገልግሎት አሰጣጥ ከፍ ለማድረግ እና ጫናዎችን ከማህበረሰቦች ላይ ለመቀነስ ያግዛል፣

6.4 ለአጋሮች፣ ለአስተባባሪ ቡድኖችና ለሌሎች ለሚመለከታቸው ተዋንያን ጠቃሚ መረጃዎችን አግባብነት ባለው የኮሙኒኬሽን ስልት ማጋራት፤

ድርጅታዊ ሀላፊነቶች

6.5 ሰብአዊ መርሆችን ሳይጥሱ ብሄራዊና የአካባቢ ባለስልጣናትን ጨምሮ ከሌሎች ጋር መተባበርንና መተጋገዝን የተመለከተ ግልፅ ቃልኪዳን በፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎች ውስጥ ማካተት፣

6.6 ከአጋሮች ጋር የሚከናወን ስራ የአጋርን የስራ ሀላፊነት፣ ግዴታዎችና ነፃነት በሚያከብሩ፤ ማነቆዎቻቸውንና ቃልኪዳኖቻቸውን ከግንዛቤ በአስገቡ ግልፅና ወጥ ስምምነቶች መመራት አለባቸው።

9በአካባቢው የሚገኙ ተዋናዮች፣ ሰብአዊ ድርጅቶች፣ የአካባቢ ባለስልጣናት፣ የግል ኩባንያዎችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ቡድኖች ጨምሮ

10 ባለስልጣናት የግጭቶች ተሳታፊ በሚሆኑበት ወቅት ሰብአዊ ተዋንያኖች ከተግባሩ ነፃነት ጋር የተገናዘበ ውሳኔያቸውን መጠቀም አለባቸው፤ በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ፍላጎቶች የውሳኔ አሰጣጣቸው ማዕከል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ።

## 7. ድርጅቶች ከልምዳቸውና ያለፈውን ከማስተዋል የሚማሩ እንደመሆናቸው በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የተሻለ የድጋፍ አቅርቦት ይደረግልናል ብለው ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡

**የጥራት መስፈርት፡-** የሰብአዊ ምላሽ ሰጪዎች በየጊዜው ከልምዳቸው ይማራሉ ፣ ይሻሻላሉ፡፡

አብይ ተግባራት

7.1 የተገኙ እውቀቶችንና የበፊት ልምዶችን በፕሮግራም ቀረፃ ወቅት መጠቀም፣

7.2 በክትትልና ግምገማ እንዲሁም በግብረመልስና ቅሬታ ላይ መሰረት በማድረግ መማር፣ መፍጠርና ለውጦችን መተግበር፣

7.3 የውስጥ ልምዶቻችንና ፈጠራዎቻችንን በአደጋ ከተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር መጋራት፣

ድርጅታዊ ሀላፊነቶች

7.4 የግምገማና የመማር ፖሊሲዎች መኖር እና ከልምድ መማሪያና አሰራርን ማሻሻያ መንገዶች መኖር፣

7.5 እውቀትንና ልምድን መመዝገቢያ ስልቶች መኖር እና በመላው ድርጅቱ ውስጥ ተደራሽ እንዲሆኑ ማድረግ፣

7.6 ሰብአዊ ምላሽን የተመለከተ ከልምድ የሚገኝ ትምህርትንና ፈጠራን ለአቻዎችና ለሴክተሩ አካላት በማጋራት ረገድ የድርጅቱ አስተዋፅኦ ማድረግ፡፡

## 8. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ብቁና በአግባቡ ከተደራጁ ሠራተኞች እና በጎ ፈቃደኞች ድጋፍ ÁÑ—K<&

**የጥራት መስፈርት፡-** ሰራተኞች [11] ስራቸውን በውጤታማ መልኩ እንዲፈፅሙ ድጋፍ ማድረግና ፍትሀዊና ከአድሎ የፀዳ አያያዝ ይደረግላቸዋል

አብይ ተግባራት

8.1 ሰራተኞች በድርጅቱ ሀላፊነትና እሴቶች እንዲሁም ስምምነት በተደረሰባቸው አላማዎችና የአፈፃፀም መለኪያዎች መሰረት ስራቸውን ያከናውናሉ፣

8.2 ሰራተኞች እነርሱን ለሚመለከቱ ፖሊሲዎች ተገዢ መሆንና ፖሊሲዎችን አለመከተል የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ጠንቅቀው ይረዳሉ፣

8.3 ሰራተኞች ሚናቸውን ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ ግለሰባዊ፣ የቴክኒክና የአስተዳደር ብቃታቸውን የሚያሳድጉና የሚጠቀሙ ሲሆን፤ ይህንን ማድረግ ይችሉ ዘንድ ድርጅቱ በምን መልኩ ሊያግዛቸው እንደሚችልም ይረዳሉ።

ድርጅታዊ ሀላፊነቶች

8.4 ድርጅቱ ፕሮግራሞችን መተግበር የሚያስችሉ የአስተዳደርና የሰራተኛ አቅምና ብቃት ያለው መሆን፣

8.5 ሰራተኛን የተመለከቱ ፖሊሲዎችና አሰራሮች ፍትሀዊ፣ ግልፅና፣ እማያዳሉና ከአካባቢው የአሰሪና ሰራተኛ ህግ ጋር የሚጣጣሙ መሆን፣

8.6 ሰራተኞች የሚጠበቅባቸውን በግልፅ መረዳት ይችሉ ዘንድ የሰራተኞች የስራ ድርሻ መዘርዝር፣ የስራ አላማዎችና የግብረመልስ ሥርዐቶች መኖር፣

8.7ሰራተኞች ቢያንስ በሰዎች ላይ ብዝበዛ፣ ጥቃትና አድልዎ እንዳይፈፅሙ ግዴታን የሚጥል የስነምግባር ደንብ መኖር፣

8.8 ሰራተኞች ክህሎታቸውንና ብቃቶቻቸውን ማሻሻል ይችሉ ዘንድ የሚደግፉ ፖሊሲዎች መኖር፣

8.9 የሰራተኞችን ደህንነትና ጤና የሚያስጠብቁ ፖሊሲዎች መኖር።

11 ሰራተኛ የሚባለው፡- ማንኛውም የተመረጠ የድርጅቱ ተወካይ ማለትም የሀገሩ ዜጋ፣ የውጪ ዜጋ፣ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ሰራተኛ እንዲሁም በጎፈቃደኛ እና አማካሪ ሊሆን ይችላል

## 9. በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች ድጋፍ የሚያደርጉላቸው ድርጅቶች ሀብቶችን በአግባቡ፣ ውጤታማነትና ስነምግባራዊነትን በተላበሰ መልኩ ይጠቀማሉ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ

**የጥራት መስፈርት፡-** ሀብቶችን በሃላፊነት በማስተዳደር እና በአግባቡ በመጠቀም ለታሰበላቸው አላማ ይውላሉ

አብይ ተግባራት

9.1 በእያንዳንዱ የሰብአዊ ምላሽ ሂደት ውስጥ አግባብነት ያለው የሀብት [12] አጠቃቀምን፣ የጥራት ምጣኔን፣ ወጪንና ወቅታዊነትን ለማረጋገጥ ፕሮግራሞችን መቅረፅና አሰራሮችን መተግበር፣

9.2 የሀብት ብክነትን በመቀነስ ሀብቶችን የታለመላቸውን አላማ ማሳካት በሚያስችል መልኩ መጠቀምና ማስተዳደር፣

9.3 ከበጀት ጋር የተናበበ የወጪ ክትትል ማድረግና ሪፖርት ማቅረብ፣

9.4 አካባቢያዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶችን በሚጠቀሙበት ወቅተ በአካባቢ ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ከግምት ማስገባት፣

9.5 የሙስና ስጋትን መቆጣጠርና ተፈፅሞ ከተገኘም ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፣

ድርጅታዊ ሀላፊነቶች

9.6 የሀብት አጠቃቀምንና አስተዳደርን የተመለከቱ ፖሊሲዎችና አሰራሮች ተዘጋጅተው መቀመጥ ያለባቸው ሲሆን የሚከተሉትን ነገሮች ድርጅቱ በምን መልኩ እንደሚፈፀም ማሳየት ያስፈልጋል፡-

ሀ. የገንዘብና የአይነት ስጦታዎችን ስነምግባራዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ መቀበልና መመደብ

ለ. ሀብቶቹን ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ መልኩ መጠቀም

ሐ. ሙስናን፣ ማጭበርበርን፣ የጥቅም ግጭቶችንና በሀብት ያለ አግባብ መገልገልን መከላከልና ምላሽ መስጠት፣

መ. ኦዲት ማድረግ፣ አግባብነትን ማረጋገጥና ግልፅ ሪፖርቶችን ማቅረብ

ሠ. ስጋቶችን በቋሚነት መገምገም፣ መቆጣጠርና መቀነስ

ረ. ሀብቶችን መቀበል ነፃነትን እንደማይሸረሽር ማረጋገጥ

12 “ሀብት” የሚለውን ቃል በሰፊ ፍቺው መረዳት ይገባል፤ ድርጅቱ ተልእኮውን ለመወጣት የሚያስፈልጉትን ነገሮች አካትቶ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ሁሉም ባይሆኑ የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው ፈንድ፣ ሰራተኛ፣ ቁሳቁስ፣ መሳሪያ፣ ጊዜ፣ የመሬት ቦታ፣ አፈር፣ ውሀ፣ አየር፣ የተፈጥሮ ውጤቶችና አካባቢ በአጠቃላይ፡፡

## ሸ. የቃላት መፍቻ

ለ CHS አላማ የሚከተሉት ፍቺዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡-

**ተጠያቂነት፡-** የተለያዩ ባለድርሻ አካላትና በቀዳሚነትም ስልጣኑን የመጠቀም ተፅእኖ ባረፈባቸው አካላት ተጠያቂ መሆንን ከግንዛቤ ባስገባ መልኩ ስልጣንን በሀላፊነት የመጠቀም አሰራር።

**በአደጋ የተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች፡-** በሆነ ስፍራ በተከሰተ አደጋ፣ ግጭት፣ ድህነት ወይም ሌላ አይነት ቀውስ የተጠቁና የተለያየ አይነት ፍላጎት፣ ተጋላጭነትና አቅም ያላቸው ሴቶች፣ ወንዶች፣ ልጃገረዶችና ታዳጊ ወንዶችን ያጠቃልላል።

**ሰነድ፡-** መባዛት የሚችል ማንኛውም አይነት የውይይቶች፣ የስምምነቶች፣ የውሳኔዎች እና/ወይም ተግባራት መዝገብ

**ውጤታማነት፡-** የድጋፍ ሥራ አላማውን ያሳካበት መጠን።

**ብቃት፡-** በግብአቶች ምክንያት የሰብአዊ ድጋፍ ፕሮግራሞች የተሳኩበት ልክ በመጠን እና በጥራት

**ተሳትፎ፡-** ድርጅቶች ፍላጎቱ ያላቸውን እና/ወይም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የሚግባቡበት፣ የሚማከሩበት እና/ወይም እንዲሳተፉ የሚደርግበት አሰራር ሲሆን የእነሱን ስጋቶች፣ መሻቶች፣ የሚጠብቋቸው ነገሮች፣ ፍላጎቶች፣ መብቶችና ምቹ እድሎች እነሱን በሚደግፉ ፕሮግራሞች ዝርጋታ፣ ትግበራና ግምገማ ወቅት በአግባቡ መጤናቸውን የሚያረጋግጥ ነው።

**ሰብአዊ ተግባር፡-** በሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ቀውሶችና አደጋዎች ወቅትና በኋላ ህይወት የማትረፍ፣ ስቃይን የመቀነስና ሰብአዊ ክብርን የማስጠበቅ አላማ ኖሮትና ችግሮቹን ለመከላከልና ለችግሮቹ ለመዘጋጀት የሚፈፀመ ተግባር ነው።

**ድርጅት፡-** CHSን መተግበር የሚያስችል የአመራር መዋቅርና ስልጣን ያለው ተቋም።

**አጋሮች፡-** ግልፅና ስምምነት የተደረሰባቸው ሚናዎችና ሀላፊነቶች ኖረዋቸው ተለይቶ የተቀመጠ ግብን ለማሳካት በይፋዊ ስምምነት ስር በጋራ የሚሰሩ ድርጅቶች።

**ፖሊሲ፡-** በፅሁፍ የሰፈረና ለውሳኔ አሰጣጥ የሚያገለግል የሃሳብ ገለፀና ደንቦች።

**ጥበቃ፡-** እድሜን፣ ፆታን፣ ብሄርን፣ ማህበራዊ፣ ሀይማኖታዊ ወይም ሌላ አይነት ዳራን መሰረት ሳያደርጉ ለሁሉም ግለሰቦች ሙሉና እኩል መብቶችን የማረጋገጥ አላማ ያላቸው ተግባራትን በሙሉ ይመለከታል። አብዛኛውን ጊዜ የደራሽ ስራ ትኩረት ከሆኑት ወቅታዊ ህይወትን የማዳን ስራዎች አልፎ ይሄዳል።

**ጥራት፡-** ሊደግፋቸው ያሰባቸውን ህዝቦች ግልፅና ታሳቢ ፍላጎቶችና መሻቶች በወቅቱ ለማርካትና ክብራቸውን ለማስጠበቅ ያለውን ችሎታ የሚያግዙ የሰብአዊ ድጋፍ ጥቅል ገፅታዎችና ባህሪያት።

**አይበገሬነት፡-** ለአደጋ የተጋለጠ ማህበረሰብ ወይም ህብረተሰብ የአደጋዎችን አሉታዊ ተፅእኖ የመቋቋም፣ የማስተናገድና ሳይዘገይ ውጤታማ በሆነ መልኩ የማገገም ችሎታ።

**ሰራተኛ፡-** ማንኛውም የተመረጠ የድርጅት ተወካይ ሲሆን የሀገሩ ዜጋ፣ የውጪ ዜጋ እና በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት የተቀጠረ ሰራተኛ እንዲሁም በጎፈቃደኛ እና አማካሪ ሊሆን ይችላል።

[13] የALNAP ምዘና የሰብአዊ ተግባር የሙከራ መመሪያ በሰጠው ፍቺ መሰረት፣ እ.አ.አ 2013፣ ገፅ 14 .

ጥራትንና ተጠያቂነትን የተመለከተው አብይ የሰብአዊ ሥራዎች መለኪያ (CHS) በሰብአዊ ምላሽ አሰጣጥ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚሰጡትን ÉÒõ ጥራትና ውጤታማነት ለማሻሻል ሊጠቀሟቸው የሚችሉ ዘጠኝ ቃልኪዳኖችን አስቀምጧል፥ ፥ ከዚህም በተጨማሪ በአደጋ ለተጠቁ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የበለጠ ተጠያቂነትን ያመቻቸ ሲሆን ይኸውም ሰብአዊ ድርጅቶቹ የገቧቸውን ቃልኪዳኖች መገንዘባቸው ድርጅቶቹን ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላቸዋል።

CHS እንደ አብይ መለኪያነቱ በመርህ ላይ የተመሰረተ፣ ተጠያቂነት ያለበትና ከፍተኛ ጥራት ያለው ሰብአዊ ተግባር ሊያሟሏቸው የሚገቡ መሰረታዊ ይዘቶችን ያብራራል። ሰብአዊ ድርጅቶች ከውስጣዊ አሰራሮቻቸው ጋር በማጣጣም በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ህግ አድርገው ሊጠቀሙት ይችላሉ።

CHS በሂውማኒታሪያን አካውንተቢሊቲ ፓርትነርሺፕ ኢንተርናሽናል፣ ፒፕል ኢን ኤይድ እና እስፌር ፕሮጀክት የተመቻቸ የ12 ወራት የሶስት ምእራፍ ምክክር ሂደት ውጤት ሲሆን በወቅቱም በመቶዎች የሚቆጠሩ ግለሰቦችና ተቋማት የአብይ ሰብአዊ ሥራዎች መለኪያውን ይዘት በጥልቀት ተንትነውና በዋና ቢሮና በመስክ ደረጃም ፈትሸውታል።


corehumanitarianstandard

@corehumstandard

www.corehumanitarianstandard.org | info@corehumanitarianstandard.org


ISBN: 978-2-8399-1564-9